02:01 ✓ ✓ ✓ •
12%

ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና...

"...እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል::"ዕብ 7:24

"ስለ እነርሱ ሊያማልድ ዘውትር በህይወት ይኖራል::" ይህን የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል በመውሰድ አንዳንዶች ጌታችንን አሁንም አማላጅ አድርገው ሲናገሩ ይሰማሉ:: ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱሳዊ እውነቱ ይህ አይደለም:: ጌታችን በመዋለ ስጋዌው (ሰው ሆኖ በምድር ላይ) የማስታረቅን ስራ ከራሱ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ፈጽሞል:: ይህ መፅሀፍ ላይ ያለ እውነት ነውና:: ግን አሁንም አማላጅ ማለት ግን ትልቅ ክህደት ነው:: ለምሳሌ በመዋለ ስጋዌው ተርቧል ተጠምቷል ክብር ይግባውና በምድር ስለ ተራበ አሁንም ረሀብተኛ ስለተጠማ አሁንም ጥማተኛ ነው አንለውም:: እንዲሁም በስጋ የማስታረቅን ስራ ስለሰራ አሁን አማላጅ አንለውም::

በመሠረቱ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከላይ ከዕብ 7፡11 ጀምሮ በደንብ ላስተዋለው ሰው አነጋገሩ በጣም ግልጽ ነው:: ሐዋርያው የኦሪትና የሐዲስ ኪዳኑን ክህነት እያነጻጸረ ነው የጻፈው፣ በሌዊ ክህነት ፍጹምነት እንዳልተገኘ የእነ አሮንም ሹመት እንዳለፈችና እንደ ምልከጼዴቅ ሌላ ካህን ማስፈለጉን በዚህም ምክንያት በመልከጼዴቅ አምሳል ሌላ ካህን ከነገደ ይሁዳ መውጣቱንና ይህም በሊቀ ካህናችን በኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸሙን ይናገራል::

ቁጥር 17 ላይም ‹‹እንደ መልከጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን አንተ ነህ›› ሲል ያስቀምጠዋል ኦሪት ደካማ ሥርዓት ስለነበረች ግዳጇን አልፈጸመችም፣ ፍጹም የሰው ልጅ ድኅነት አልተገኘባትም ነበር ካህኑ ለኃጢዓት ማስተሰርያ እንሰሳትን መስዋዕት አድርጎ የሚረጨው ደም የአዳምን የውርስ ኃጢዓት ሊያነፃ በፍጹም አልቻለም ነበርና በእሷ በኦሪት ፈንታ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ተስፋ ገብቷል እያለ ነው ቅዱስ ጳውሎስ የሚያብራራው ከታች ዝቅ ብሎ ከቁጥር 24 ጀምሮ

‹‹እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው ስለ እነርሱም ለማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ

ጀምሮ
‹‹እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው ስለ እነርሱም ለማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል እንደ እዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባልና እርሱም እንደነዚያ (እንደኦሪቶቹ) ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለራሱ ኃጢዓት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢዓት ዕለት ዕለት መስዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና›› (ዕብ 7፡27) ለነገሩ ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መናፍቃኑ ለምንፍቅና ትምህርታቸው እንዲመቻቸው ‹‹ስለ እነርሱ ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል›› ብለው ያጣሙት እንጂ ቆየት ብሎ በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ (1960) ላይ ግን እንደዚህ አይደለም የተቀመጠው ትክክለኛው ቃል
‹‹ክህነቱ አይሻርምና ዘወትር በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ሊያድናቸው ይቻለዋል ለዘላለም ሕያው ነውና ያስታርቃቸዋል›› ነው የሚለው (ዕብ 7፡24-25) ይህስ ቢሆን ምን ማለት ነው?
ጌታችን ራሱ መስዋዕት አቅራቢ ራሱ መስዋዕት ፣ ራሱ መስዋዕት ተቀባይ ሆኖ አንድ ጊዜ ብቻ ራሱን ባቀረበው መስዋዕት ለዘላለም ኃጢዓታችንን ያስተሰርይልናል።
አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደም ያለፈውንም ሆነ የሚመጣውን ትውልድ ለዘላለም ያስታርቀዋል እንጂ እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው

‹‹ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም››
ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና ስለዚህ እኛም ፍጹም ድኅነትን ያገኘነው አንድ ጊዜ በሠራልን የክህነት ስራ ነው በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድራዊ ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷል (ቆላ 1፡19) ተብሎ እንደተጻፈ ይህ የሠራልን የክህነቱ ሥራው ነው ዘወትር ሲያስታርቀን የሚኖረው አሁንም ያማልደናል ካልን ግን ክርስቶስ ዕለት ዕለት ኃጢዓት በሠራን ቁጥር መሞት አለበት ማለት ነው። ምክንያቱም ዓለም ፍጹም ድኅነት ያገኘችው በእርሱ ሞት ብቻ ነውና ! ወይም በሌላ አገላለጽ እንዲህ ማለት ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስ አንካሳውን ሰውዬ ‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ›› ሲለው ተነሥቶ ተመላልሷል ጴጥሮስ ‹‹ተነሣና ተመላለስ›› ብሎ ሲናገር አንድ አንካሳ ብቻ ዳነ እንጂ ለዚህ አንከሳ የተነገረው ቃል በጴጥሮስ እጅ ሊተፈወሱ ሌሎች ብዙ አንካሶች

‹‹ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም››
ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና ስለዚህ እኛም ፍጹም ድኅነትን ያገኘነው አንድ ጊዜ በሠራልን የክህነት ስራ ነው በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድራዊ ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷል (ቆላ 1፡19) ተብሎ እንደተጻፈ ይህ የሠራልን የክህነቱ ሥራው ነው ዘወትር ሲያስታርቀን የሚኖረው አሁንም ያማልደናል ካልን ግን ክርስቶስ ዕለት ዕለት ኃጢዓት በሠራን ቁጥር መሞት አለበት ማለት ነው። ምክንያቱም ዓለም ፍጹም ድኅነት ያገኘችው በእርሱ ሞት ብቻ ነውና ! ወይም በሌላ አገላለጽ እንዲህ ማለት ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስ አንካሳውን ሰውዬ ‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ›› ሲለው ተነሥቶ ተመላልሷል ጴጥሮስ ‹‹ተነሣና ተመላለስ›› ብሎ ሲናገር አንድ አንካሳ ብቻ ዳነ እንጂ ለዚህ አንከሳ የተነገረው ቃል በጴጥሮስ እጅ ሊተፈወሱ ሌሎች ብዙ አንካሶች አልሠራም ማለትም ለሁሉም አንካሶች እንደገና ለእያንዳንዳቸው ‹‹ተነሣና ተመላለስ›› ተብሎ መነገር አለበት። ይህ የሚያሳየው በፍጡራን አንድ ጊዜ የተነገረው ቃል ሥራ የሚሰራው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ማለት ነው።

የፈጣሪ ቃል ግን እንዲህ አይደለም ፈጣሪ አንድ ጊዜ የተናገረው ቃል ለዘላለም ጸንቶ ነው የሚኖረው ለምሳሌ እግዚአብሔር ዓለሙን ሲፈጥር "ይሁን ይሁን" እያለ የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ይኸው አንድ ጊዜ በተናገረው ቃል እስከ ዕለተ ምጽዓት "ሁኑ" እንዳላቸው ሆነው ተገኝተዋል ‹‹ቀንና ሌሊት ይለዩ›› (ዘፍ 1፡14) ብሎ አንድ ጊዜ ብቻ በተናገረው ቃሉ ይኸው ቀንና ሌሊት እየተፈራረቁ ነው ይህም በፈጣሪ አንድ ጊዜ የተነገረው ቃል ዘላለማዊ ሥራ እንደሚሠራ ነው የሚያሳየን " (1) እናም ‹‹ለዘላለም ሕያው ነውና ያስታርቃቸዋል›› ወይም መናፍቃኑ እንደሚሉት ‹‹ሲያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል›› ተብሎ ቢነገረም እንኳን ትርጉሙ ከዚዘሀ ከላይ ካየነው የተለየ አይደለም ‹‹ራሱን መስዋዕት አድርጎ ባቀረበ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎልናልና›› እንደተባለው ጌታችንም ‹‹የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው›› ብሎ ማስታረቅን ያጠቃለለበት ያው አንዴ የተናገረው የምልጃ ቃል ክርስቶስ ደጋግሞ ሳያማልድ የሚመጣውንም ሁሉንም ትውልድ የሚያስታርቅ ነው።

"ተፈጸመ" ያለውም ይህንኑ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታረቀበትን ሥራ ነው

"ተፈጸመ" ያለውም ይህንኑ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታረቀበትን ሥራ ነው ያው አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ የተነገረ ቃል የአምላክ ቃል ነውና ለዘወትር ይጸናል። ልክ እግዚአብሔር ‹‹ቀንና ሌሊት ይለዩ›› ብሎ አንዴ በተናገረው ቃል መሠረት ቀንና ሌሊት እየተፈራረቁ እስከ ዕለተ ምጽዓት ድረስ እንደሚቆዩት ማለት ነው ከዚህ ውጪ ግን ክርስቶስ ያን በሞቱ አንድ ጊዜ የፈጸመውን የማዳን የማስታረቅ ሥራ አሁንም ይሠራል ብሎ ማመን ከኑፋቄም በላይ ክህደት ነው የእግዚአብሔርንም ፍቅሩን አለማወቅም እኛም አልዳንም ክርስቶስም እንደገና መጥቶ መሞት አለበት ማለት ነው። በአጠቃላይ ሐዋርያት የክርስቶስን ስም ከምልጃ ጋር ቢጠቅሱም እንኳን እስካሁን ባየነው መልኩ ነው መታየት ያለበት ከዚህ ውጪ ግን ራሱ ጌታችን ለሐዋርያት በዚያች ቀን (ከትንሣኤ በኋላ) **ዮሐ 16:26** "በስሜ ትለምናላችሁ እኔም ስለ እናንተ አብን አለምንም" ብሏቸው እያለ ‹‹አይ አንተ ከትንሣኤህ በኋላ ታማልዳለህ›› ብለው አይቃወሙትም ‹‹ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ›› ያላቸውን አምላክ ጠንቅቀው ያውቁታል ደግሞስ ቅዱስ ጳውሎስ **2ቆሮ 5:16-18** ‹‹ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ በሥጋው ወራት እንደምናውቀው ከእንግዲህ ወዲያ እኛም ሐዋርያቱ ብንሆን በሥጋ እንዳወቅነው አናውቀውም›› በማለት ነው የጻፈው እንዲያውም እዚያው ላይ ቁጥር 19 ጀምሮ ‹‹በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ፣ የማስታረቅን ሥልጣን ለእኛ ሰጠን እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ዕወቁ›› ነው ያለው።

በመሆኑም የክርስቶስ የማስታረቅ ሥራ የማማለድ አገልግሎት በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ በመስዋዕትነት ተፈጽሟል።
‹‹ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን (ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ) ጋር በሥልጣን፣ በአገዛዝ፣ በሕልውና አንድ ስለሆኑ) የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር (የሦስትነትና የአንድነት ስማቸው) ነው አንድም ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር ነው፣) እግዚአብሔር ‹‹በክርስቶስ ሆኖ›› (ሥጋን ለብሶ ሰው ሆኖ) ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር›› (ጎላፊ ቃል) በደላቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበር በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን እናማልዳለን›› (2ቆሮ 5፡18-21)

ራሱ እግዚአብሔር ነው፣) እግዚአብሔር ‹‹በክርስቶስ ሆኖ›› (ሥጋን ለብሶ ሰው ሆኖ) ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር›› (ጎላፊ ቃል) በደላቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበር በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን እናማልዳለን›› (2ቆሮ 5፡18-21)

በሌላ አገላለጽ
ቅዱስ ጳውሎስ ለምን እንዲህ ፃፈ ብንል "በምድር ላይ አንድ ጊዜ የፈፀመውን የማስታረቅ ተግባርን ለመግለፅ ነው።" እንዴት ብንል መፅሐፍት ምስጢርን እንጂ የአፃፃፍ ዘይቤን ጠብቀው ስላልተፃፉ ነው። ይህም ያለፉና የተፈፀሙ ድርጊቶችን ወደ ፊት የሚፈፀሙ አስመስለው ይፅፋሉ። ወደፊት የሚፈፀሙትን ተግባራት ደግሞ ያለፉ አስመስለው ይፅፋሉ። እንዲሁም አንድ ጊዜ የተፈፀሙትን ወደፊት ቀጣይነት ያላቸው አስመስሎ መፃፍ የመፅሐፍት ባህሪ ነው። በምሳሌ እንመልከት።
ኢሣ 65÷17 "እነሆ አዲስ ሰማይ እና አዲስ ምድር እፈጥራለው።" ይህ ቃል እግዚአብሔር ፈጥሮ ያዘጋጃትን አዲስ ሰማይና ምድር የተባለችውን መንግስተ ሰማይን ወደፊት እንደሚፈጥር አስመስሎ ይናገራል።
ኢሣ 53÷1 ላይ ደግሞ ጌታችን ሳይወለድ 700 ዓመት በፊት መከራን ሳይቀበል መከራን እንደተቀበለ አድርጎ ፅፎታል። እንዲሁም
ኢሣ 9÷6 ላይም ክርስቶስ ሳይወለድ እንደተወለደ አድርጎ ይናገራል።
ይሁዳ 1÷7 "እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ስጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸው የነበሩ ከተሞች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።"
ሰዶም እና ገሞራ አንድ ጊዜ ተቀጥተው እንደጠፉ በዘፍ 19 ተፀረፏል። ነገር ግን ይህ ተግባር ቀጣይነት ያለው ተግባር በሚመስል መልኩ ተፅፏል። "እየተቀጡ " ብሎ።
ስለዚህ በዚህ መሰረት በዕብ 7÷25 ላይም አንድጊዜ የተፈፀመን የማማለድ ተግባርን ቀጣይነት ያለው አስመስሎ ተፅፏል። ፈጥሮ እፈጥራለው፣ ሳይወለድ ተወለደ፣ ተቀጥተው እየተቀጡ ካለ አማልዶም ሊያማልድ ቢል ይህ የመፅሐፍት የአፃፃፍ ባህሪ ነው።